*ኢትዮጵያ ግብጽ አይደለችም- አንድ ተብሎ የሚጀመረዉ*

*ናኦሚ በጋሻዉ*
*ሎንግ ቢች ካሊፎርኒያ*
*(naomibegashaw@gmail.com)*

*ኤፕሪል 3 2011*

*በግብጽና በቱኒዚያ የታየዉን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እንደ ምሳሌ በመጥቀስ፣ ድርጅታዊ ሥራ ሳይሰራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዛሬ ነገ ሊነሳ ይችላል ብለዉ ብዙዎ ይጠባበቃሉ። እነዚህ ሰዎች እንደጠበቁትም ሕዝቡ ሊነሳ ይችላል። የወደፊቱን እንዲህ ነዉ ብሎ በርግጠኝነት ለመተንበት ይከብዳል። ነገር ግን ያለዉን ሁኔታ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ስናያቸዉ አሁን ባለዉ ሁኔታ ሕዝቡ የሚነሳ አይመስልም።*

*አንዳንዶች ደግሞ በአገር ቤት ያሉ ድርጅቶች በዚህ ወቅት ሕዝቡ እንዲነሳ ጥሪ ባለማቅረባቸዉ ጠንከር ያለ ትችት ያቀርቡባቸዋል።*

*ሕዝብ እንዲሁ በባዶ ሊነሳ አይችልም። ድርጅታዊ ሥራ ያስፈልጋል። ድርጅታዊ ሥራ ስል የፖለቲካ ድርጅታዊ ሥራ ብቻ ማለቴ አይደለም። በትምህርት ቤቶች፣ በቀበሌዎች፣ በሲቪክ ማህበራት፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በኢንተርኔት … የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ዜጎች መሰባሰብ አለባቸዉ። በዚህም ሆነ በዚያ ሕዝባዊ ሕዝቡ ካልተሰባሰበና ካልተደራጀ እንቅስቃሴዎች ሊኖሩ አይችሉም።*

*በግብጽና በቱኒዚያ የተነሳዉ እንቅስቃሴ እራሳቸዉን በይፋ ገሃድ ባላወጡ ወጣቶች የተጀመረ እንቅስቃሴ ነዉ። በኢራን ተከስቶ በነበረዉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተበረታተዉ፣ ወጣት ቱኒዚያዉያንና ግብጻዉያን ከአመት በላይ ሕዝቡን በትዊተርና በፌስቡክ ሲያደራጁት፣ የመገናኛ መረብ ሲዘረጉ ቆይተዋል። የግብጽና የቱኒዚያ ንቅናቄ ሥራ ተሰርቶበት የተገኘ ዉጤት እንጂ በድንገት የመጣ አይደለም። ይህንን ኢትዮጵያዉያን መገንዘብ ያለብን ይመስለኛል።*

*ኢሕአዴግ ሕዝብን የሚያሰባስቡና የሚያገናኙ መድረኮችንና ተቋማትን ማፈራረሱን ቀንደኛ ተግባሩ አድርጎ ነዉ የወሰደዉ። ገለልተኛና ጠንካራ የሲቪክ ማህበራት ኢትዮጵያ ዉስጥ በአሁኑ ጊዜ የሉም። በየጊዜዉ እሁድ በአብያተ ክርስቲያናት አርብ ደግሞ በመስጊዶች ሕዝብን የሚያሰባስቡ የሃይማኖት መሪዎች፣ በእግዚአብሄር ስም ህዝቡ አንገቱን እንዲደፋ ለመብቱ እንዳይቆም፣ ለፍትህ እንዳይሰለፍ እያደረጉት ነዉ። በተዘዋዋሪ መንገድ ገዢዉ ፓርቲ እነዚህን የሃይማኖት ተቋማት የመብትንና የፍትህን ጥያቄ በማንሳት አንጻር ሽምድምድ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።*

*ሌሎች እንደ መምህራን ሰራተኞች ማህበር አይነቶችን ደግሞ የራሱ ካድሬዎችን በቦታዉ በማስቀመጥ የሰራተኛዉን መብት በማስከበር ላይ ሳይሆን የገዢዉ ፓርቲ ጥቅም በማስጠበቅ ላይ እንዲሰማሩ የተደረጉበት*

*ሁኔታ ነዉ ያለዉ። በርግጥም «ይሄ ነዉ» የሚባል ገለልተኛ የሲቪክ ማህበር በኢትዮጵያ ዉስጥ በአሁኑ ጊዜ አይገኝም።*

*በግብጽ 11 ሚሊዮን ሕዝብ ቀጥታ የስልክ መስመር ሲኖረዉ፣ የሞባይል ተጠቃሚ የሆነዉ ደግሞ 56 ሚሊዮን ይደርሳል። ከሰባ በመቶ በላይ የግብጽ ሕዝብ በስልክ የተገናኘ ነዉ። በቱኒዚያ 1.2 ሚሊዮን የሚሆነዉ ህዝብ ቀጥታ የስልክ መስመር አለዉ። 9.7 በመቶ ሚሊዮን የሞባይል ተጠቃሚ ነዉ። በጥቅሉ ከ99.5 በመቶ በላይ የቱኒዚያ ሕዝብ በስልክ የተገናኘ ነዉ። ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ስንመለስ ቁጥሩ ማሳፈር ብቻ ሳይሆን አሳዛኝ ነዉ። ቀጥታ የስልክ መስመር ያላቸዉ ኢትዮጵያዉን 915 ሺህ ብቻ ናቸው። ከአንድ ሚሊዮን ያነሰ ማለት ነዉ። 4 ሚሊዮን የሚሆኑ የሞባል ተጠቃሚዎች ብቻ ነዉ ያሉት። በአጠቃላይ 5.5 በመቶ ብቻ የሚሆነዉ ህዝባችን ነዉ በስልክ መገናኘት የሚችለዉ።*

*ወደ ኢንተርኔት አገልግሎት ስንሄድ በግብጽ 21 ሚሊዮን ህዝብ ( 27 በመቶ ) በቱኒዚያ ደግሞ 4 ሚሊዮን ህዝብ (40 በመቶ) የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ነዉ። በኢትዮጵያ 447300 ሺህ ወይንም 0.4 ሚሊዮን ህዝብ (0.4 በመቶ) ብቻ ነዉ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኘዉ። በግብጽና በቱኒዚያ በርካታ የቴሎኮሚኒኬሽን ኩባኒያዎች በመኖራቸዉ ሕዝቡ በቀላሉ በፌስቡክ በትዊተር ለመገናኘትና እራሱን ለማደራጀት ችሏል። በኢትዮጵያ 0.4 በመቶ ሕዝብ ብቻ ተጠቃሚ በሆነበት ሁኔታ ፣ ያዉም ደግሞ ብዙ ድህረ ገጾች እየታፈኑ፣ ሕዝቡን በኢንተርኔት ብቻ ማደራጀት አይቻልም። በግብጽ በቱኒዚያ ለዉጥ ያመጣዉ የፌስቡካና የትዊተር እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ብቻዉን ብዙ ለዉጥ ሊያመጣ አይችልም።*

*በግብጽና በቱኒዚያ ሌላዉ ትልቅ ለዉጥ ያመጣዉ በአገሪቷ ያሉት መንግስት የማይቆጣጠራቸዉ በርካታ የሳተላይት ቴሌቭዥኖች ናቸዉ። በግብጽ መንግስት ከሚቆጣጠረዉ ቴሌቭዥን ጣቢያ ዉጭ ወደ ሃያ የሚሆኑ የግል ሳተላይት ቴሌቭዥን ጣቢያዎች አሉ። በመለዉ ግብጽ የሚሰሙ ሁለት የግል ራዲዮ ስርጭቶች የሕዝቡን ጥያቄዎች ሲያትቱ ነበር።*

*በአገራችን ኢትዮጵያ ገዢዉ ፓርቲ የሚቆጣጠረዉ አንድ የቴሌቭዥን ጣቢያ ነዉ ያለዉ። ከፖለቲካ ዉጭ አዝናኝ ዘገባዎችና ፕሮግራሞች የሚያቀርቡ ኤፌም ሬዲዮዎች ቢኖሩም፣ ከሞላ ጎደል በገዢዉ ፓርቲ ስር የሆኑ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሬዲዮና የፋና ሬዲዮ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሰራጩ ብቸኛ የራዲዮ ጣቢያዎች ናቸዉ ማለት ይቻላል።*

*የሳተላይት ዲሽ ያላቸዉ ከአንድ በመቶ የማይበልጡ ኢትዮጵዉያን ይኖራሉ። እነዚህ ኢትዮጵያዊያን ከኢቲቪ ዉጭ እንደ ኢሳት ያሉ የቴሌቭዥን ጣቢያዎችን ሊሰሙ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን አንድ በመቶ ህዝብ ብቻ የሳተላይት ተጠቃሚ በሆነበት ሁኔታ በግብጽና በቱኒዚያ የአረብ ሳተላይቶች ዉጤት እንዳመጡት፣ ኢሳት በኢትዮጵያ ዉጤት ሊያመጣ ይችላል ማለት ትንሽ አስቸጋሪ ነዉ።*

*ይህን የምጽፈዉ በኢትዮጵያ ለዉጥ እንዲመጣ እንታገላለን የሚሉትን ተስፋ ለማስቆረጥ አይደለም። ነገር ግን ያለዉን ተጨባጭ ሁኔታ ተረድተን ኢትዮጵያ ካለችበት ሁኔታ ጋር የሚመጠን እንቅስቃሴዎችን ማድረግ እንድንጀመር ነዉ እንጂ።*

*ይህንን ዉይይት የበለጠ ለማስፋት አንዳንድ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የመጀመሪያዉን ክፍል አጠቃልላለሁ። እነዚህም ጥያቄዎች በብዛት በፖለቲክ ድርጅቶች ላይ ያተኮረ ነዉ።*

- *ገዢዉ ፓርቲ ሕዝቡ እንዳይደራጅ ስር የሰደደ የአፈና መረብ ዘርግቷል። ሕዝቡን ለማደራጀትና ለማስተባበር የራሱ የሆነ ትልቅ ጥረት ይጠይቃል። አሁን ባለዉ ሁኔታ ሕዝቡን ለማደራጀት የሚችል የትኛዉ ድርጅት ነዉ ?*

- *በአገር ቤት እንደ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) ያሉ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ድርጅቶች ተስፋ የሚጣልባቸዉ ድርጅቶች ናቸዉ ወይ ?*

- *በአገር ቤት ያሉ ድርጅቶች የደከሙ ናቸዉ የምንል ከሆነ፣ እነዚህ ድርጅቶች እንዲጠነክሩ ማድረግ አይቻልም ወይ ? አይ እነርሱን መተዉ ነዉ ከተባለስ ሕዝቡን ሊያደራጅ የሚችል ሌላ ድርጅት ማን የቱ ነዉ?*

- *አመራራቸዉ ዉጭ አገር የተቀመጡ ድርጅቶች ላይ ተስፋ የሚጥሉ አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን አሉ። በእዉኑ ጽ/ቤታቸዉ አስመራ፣ ዋሺንግትን ዲሲ፣ ለንደን …የሆኑ ድርጅቶች በአገር ቤት ሕዝቡን ማደራጀት ይችላሉን?*

*በሚቀጥሉት ክፍሎች ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሆናሉ የምላቸዉን አንዳንድ ነጥቦች ለማስፈር እሞክራለሁ። እስከዚያዉ ሁላችንም ባለንበት ቸር ይግጠመን።*